Department of Accountability and Research

Alexandria City Public Schools
1340 Braddock Place, 3rd Floor
Alexandria, Virginia 22314

Phone: 703-619-8032
accountability@acps.k12.va.us
www.acps.k12.va.us/accountability

ውድ ወላጆች/አሳዳጊዎች:

አብዛኛዎቹ - በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ACPS) ውስጥ በሦስተኛ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ የ‘Naglieri Nonverbal Ability Test – Third Edition (NNAT3)’ ፈተናን ይወስዳሉ። ይህ ደብዳቤ፤ የዚያን ፈተና ውጤቶች ለእናንተ የሚያቀርብ - የ**“NNAT3 Home Report”**ን አብር-የያዘውን - ይህም የየግል የተማሪ ውጤቶችን - የያዘ ነው።

ለውጤቶቹ፣ እንዴት ትርጓሜ መስጠት እችላለሁ?
የ‘**NNAT3 Home Report**’፣ በ‘NNAT3’ ላይ የልጅዎን የክንውን ሂደቶች ያሳያል። ውጤቶቹም መመልከት እና መገንዘብ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። በመጀመሪያ፤ የተማሪውን መረጃ የያዘውን፣ በገጹ ከላይኛው ከፍል ላይ ያለው የተማሪው ስም፣ ዕድሜ እና ትምህርት ቤት ትክክል መሆኑን አረጋግጡ። በሁለተኛነት፤ ከሪፖርቱ-መካከል ላይ፣ የውጤት ደረጃዎችን-በያዙት ሁለት ካሬዎች (squares) በመጀመር፣ ለ'**Naglieri Ability Index**’ እና ለ‘**Percentile Rank**’፤ተማሪዎ ያገኘውን/ያገኘችውን የውጤት ደረጃዎች ተመልከቱ።

‘**Percentile Rank**’፣ በጣም ጠቃሚ የሆነ የውጤት-ደረጃ ሊሆን የሚችልበት ነው። ይህ የብሄራዊ የመቶኛ (percentile) የውጤት ደረጃ ሲሆን፤ በአንድ-ዓይነት የዕድሜ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ከሃገሪቱ ሌሎች ልጆች ዙሪያ በማነፃፀር፣ የልጅዎን ትክክለኛውን ውጤት የሚያሳይ ነው። የመቶኛ ውጤቶቹ (Percentile scores)፣ ከ1 እስከ 99 ድረስ ባለው ውስጥ ሲሆን፣ እና የብሄራዊ አማካኙ (national average) ደግሞ፣ 50 ነው። ተማሪው የመቶኛ ደረጃው (Percentile Rank)፣ 55 ከሆነ፤ ይህ የሚያመለክተው፣ ተማሪው 55% ከሆኑ በእድሜው/ዋ የሚገኙ ተማሪዎች እኩል በጥሩ ሁኔታ ወይም በተሻለ-ሁኔታ ሰርቷል/ታለች ማለት ነው። የልጅዎ የውጤት ደረጃ ከብሄራዊ አማካኝ (national average) በላይ ወይም በታች እንደሆነና እንዳልሆነ አረጋግጡ። የተሰጠው ውጤት፣ ስለተማሪዎ በምታውቁት ነገር ላይ በትክክለኛ ሁኔታ ይስማማ እንደሆነ እንዳልሆነ እራሳችሁን ጠይቁ።

የ‘**Naglieri Ability Index**’፣ በመቶኛ ደረጃው (Percentile Rank) ላይ ከታየውን ውጤት ጋር አንድ-ዓይነት ውጤትን የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ ነገር ግን በተለይ መመዘኛ ላይ ይመዘናል። የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ውጤቶቻቸው፤ በ90 እና 110 መካከል ውስጥ ይገኛል። ተማሪዎ እንዴት ደረጃውን እንዳመጣ፣ በዳይመንድ (diamond) የተለየውን፣ በዕድሜያቸው ያሉ ተማሪዎች ብሄራዊ ናሙና ጋር በማነፃፀር - በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት፣ ከሁለቱ ካሬዎች (squares) በላይ ያለውን ግራፍ (graph) መጠቀም ትችላላሁ። የመግለጫ ገደቦቹ (Description ranges)፤ (ለምሳሌ፤ “ዝቅተኛ አማካኝ/Low Average” ወይም “አማካኝ/Average”) ተብለው የተሰጡት፤ በልጅዎ የክንውን-ችሎታ ላይ አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖርዎ ለመርዳት ሲባል ነው። የተመደቡት የውጤት የደረጃ መጠኖቹ (score ranges) እና መግለጫዎቹ (Descriptions)-እራሳቸው፤ ፍፁም አይደሉም።

የፈተና ውጤቶቹ፣ በተለያዩ መንገዶች - በአስተማሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ እና ወላጆች በጥቅም-ላይ ሊውል ይችላል፤ ሆኖም-ግን፣ የተለመደ-የማጣቀሻ ፈተናዎች (norm-referenced tests) የሆኑት፤ እንደ ‘NNAT3’ያሉት፤ ተማሪዎች በ30 ደቂቃ ግምገማ ሊያሳዩት በሚችሉት፣ ያለ-ንግግር ቋንቋ የችሎታ ብቃቶች (nonverbal abilities) በመለካት ላይ ውስንነትን ያሳያሉ። ምንም ዓይነት ፈተና ወይም የፈተና ፕሮግራም፤ ለሁሉም ግለሰብ 100% ትክክለኛ ሊሆን አይችልም። የክፍል-ውስጥ አስተማሪው አስተያየት፤ የተማሪውን የችሎታ ብቃት ምናልባት በይበልጥ ሊጠቁም ይችላል።

ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባካችሁን የልጃችሁን አስተማሪ፣ ካውንስለር፣ ወይም ርዕሰ-መምህር ያነጋግሩ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባካችሁን ወደ ቢሮአችን በ703-619-8032 ደውሉ።

ከሰላምታ ጋር፣



ዶ/ር ክሊንተን ፔጅ (Dr. Clinton Page)
የተጠያቂነት እና ምርምር ዋና-ሹም/Chief Accountability and Research Officer